## Smittskydd Skåne

# ኤችአይቪ

*የበሽተኞች መረጃ: መብቶችና መመሪያዎች*

### ኤችአይቪ ምንድነው?

ኤችአይቪ: በአካል የመከላከያ ተቅዋም ተጽኖ የሚያደርግ የኢንፌክሽን በሽታ ነው። አብዛኞቹ በበሽታው የተለከፉ ግለሰዎች: የበሽታው ተሸካሚዎች መሆናቸው አያውቁም። አንዳንዶቹ ግን በበሽታው ከተለከፉ ከ1 እስከ 4 ሳምንቶች በህዋላ ይመማሉ፤ ላጪር ጊዜ ትኩሳት ይታይባቸዋል፤ የጉሮሮ ህመም ይይዛቸዋል፤ የሊምፍ እብጠት ይከሰትባቸዋል፤ በቆዳቸው ሽፍታ ይወጣባቸዋል። ይህ የኢንፌክሽኑ የመጀመሪያ ደረጃ ነው። ከጥቂት አመታት በህዋላ የመከላከያ ተቅዋሙ ሲዳከም: ሌሎች የበሽታ ምልክቶች ይከሰታሉ። ቆይቶም የኢንፌክሽን ሕመሞችና ካንሰር ይታዩና በኤይድስ የሚታወቀውን በሽታ ይከተላል። መድኃኒት መጠቀም በአካል ያለውን የቫይረስ መጠን ይቀንሰውና ወደ ኤይድስ እንዳይለወጥ ሂደቱን ያዘገየዋል። የኤችአይቪ ኢንፌክሽን በፍጹም አይድንም። በሽታው ያለበት ሰው መላው ህይወቱ ቫይረሱን ተሸክሞ ይኖራል። መድኃኒት እየወሰደም በሽታው ወደ ሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ ይችላል።

### የበሽታ ማስተላለፊያ መንገዶች

ኤችአይቪ በግብረ-ሥጋና በደም ይተላለፋል፤ አንድ የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ያላት እናት: በርግዝና: በግልግልና ስታጠባ ወደ ልጅዋ ማስተላለፍ ትችላለች። የኤችአይቪ የጾታ ኢንፌክሽን: በብልት: በአፍና በፍንጥጣ የሚፈጸመው ግብረ-ሥጋ ይተላለፋል። በደም የሚተላለፍ ኢንፌክሽን አንድ ሰው ለሌላ ሰው ደም ሲሰጥ (ትራንስፉዥን) ሊከሰት ይችላል፤ በተጨማሪም ኤችአይቪ ያለው ግለሰው የተጠቀመበት መርፌ ሌላ ሰው ከተወጋበት ወይንም አንድ ግለሰው ከሌላ በጋራ መርፌ ከተጠቀመ ኢንፌክሽኑ ሊተላለፍ ይችላል። ኤችአይቪ ያለበት ደም በአይን: በአፍ ካለው መምብሬን (slemhinna) ከተነካካ: ወይንም በቆዳ የሚከሰት ቁስል ኮንታክት ካደረገ: የኢንፌክሽን አደጋ አለ። ህክምና የኤችአይቪን የመተላለፍ ችሎታ ይቀንሳል፤ ቢሆንም የኢንፌክሽን የማስተላለፍ አደጋ አያስወግድም።

### ኤችአይቪ እንዴት ይተላለፋል?

ኤችአይቪ በመተቃቀፍ: በመሳሳምና በእንባ አይተላለፍም። ተቅማጥ: ሽንት: ትውከት ወይም ደም የሌለበት ምራቅ አያስተላልፍም። ባልቆሰለ ቆዳ የነጠበ ደምም የኢንፌክሽን አደጋ አያስከትልም።

### መብቶች

በስዊድን ኢንፌክሽን ህግ መሠረት (smittskyddslagen): ምርመራ: የሀኪም ቀጠሮና ህክምና ለሁሉም በሽተኞች ከክፍያ ነጻ ነው። በሽታዎን እንዲችሉ የሚያስፈልግዎት የሳይኮ-ማህበራዊ ድጋፍ ያግኙ ዘንድም መብት አለዎት። ለሌሎች ሰዎች የኢንፌክሽን የማስተላለፍ አደጋ እንዳያጋልጡ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ሀኪምዎ ምክር ሊሠጥዎት ይችላሉ።

### የሙያ እንቅስቃሴ

የኤችአይቪ ኢንፌክሽን በመደበኛው የሙያ ኑሮዎና በትምህርትዎ እንቅፋት አይሆንብዎትም። ኤችአይቪን የማስተላለፍ አደጋ ቢኖር: አንዳንድ ጊዜ በሥራና በፕራክቲክ ወይንም በሌላ እንቅስቃሴ የመሳተፍ እድልዎን ሊቀንሰው ይችላል።

### እርግዝናና ልጅ ማጥባት

እንደ የኤችአይቪ ቫይረስ ተሸካሚ መጠን: በጣም ትንሽ በሆነ አደጋ: የኤችአይቪ በሽታ ከሌለበት ባለቤትዎ ልጅ እንዲወልዱም አገዝ ሊሠጠዎት ይችላል። የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ያላቸው እናቶች ማጥባት የለባቸውም።

### ልጆችና ኤችአይቪ

የኤችአይቪ ተሸካሚ ልጆች: ልክ እንደ ሌሎች ልጆች የእንክብካቤና የትምህርት መብት አላቸው። ቢሆንም በግምት ውስጥ መግባት ያለበት ልዩ ፍላጎት ሊኖራቸውም ይችላል። ልጆች ባጸደ ህፃናትና ባንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምን ዓይነት መመሪያ መከተል እንዳለባቸው ሀኪሞች ወላጆችንና አሳዳጊዎችን ማሳወቅ አለባቸው። ስለ አንድ ኤችአይቪ ያለበት ልጅ አስመልክቶ ባጸደ ህፃናትና ባንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

## Smittskydd Skåne

ላሉት ሠራተኞች መረጃ ለመሥጠት የወላጆችና ያሳዳጊዎች ፈቃድ ያስፈልጋል። ወላጆች/አሳዳጊዎችና እንዲሁም ልጆች ከዕድሜ የሚስማማ ኢንፌክሽን የመከላከል መረጃ በየጊዜው ህክምና ከሚሠጠው ሀኪም ያገኛሉ።

### የአፍ: የብልትና: የፍንጥጣ ግብረ-ሥጋ በሚፈጸምበት ወቅት ኮንዶም መጠቀም

ኮንዶም: የኤችአይቪ ኢንፌክሽንና የሌሎች በግብረ-ሥጋ የሚተላለፉ ህመሞችን በመከላከል ረገድ ጥሩ የሆነ አግባብ ነው። ወሲብ ተጀምሮ እስኪፈጸም ኮንዶም መጠቀም ይገባል። የሴቶች ኮንዶምም ቢሆን ከኢንፌክሽን ይከላከላል የሚል ግምት ቢኖርም: በሳይንሳዊ አግባብ እስካሁን ድረስ አልተረጋገጠም።

### ኢንፌክሽን ለመከላከል የሚደረግ መድሃኒታዊ ህክምና

ኮንዶም ተጠቅሞ ሲያበቃ: ባጠገብዎ የሚገኝ ሰው በወሲብ ወይንም ከደምዎ ነጥቦበት ወይም በሌላ አግባብ ለኤችአይቪ ኢንፌክሽን ከተጋለጠ: ኢንፌክሽን ለመከላከል መድኃኒታዊ ድኅረ-ህክምና (postexpositionsprofylax (PEP)) ሊደረግለት ይችላል። ይህ ዘዴ ወዲያውኑ መጀመር አለበት። ሀኪሙን ወይም ክሊኒኩን ጊዜ ሳያጠፉ ያነጋግሩ።

### የኢንፌክሽኑን ምንጭ መፈለግ

አንድ ግለሰው ምንም ምልክቶች ሳይታዩበት የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ሊኖረው ስለሚችል: በኢንፌክሽኑ የተለከፉ ግለሰዎች መፈለግ አስፈላጊ ነው። የኢንፌክሽን ምንጭ እንዲገኝ የመሳተፍ ግዴታ አለብዎት። የዚህ ዋና ዓላማ ጉዳት ለመቀነስና በሽታው ወደ ሌሎች ግለሰዎች እንዳይሰራጭ ለመከላከል ነው። የኢንፌክሽን ምንጭ መፈለግ ማለት: ምንጩ ለማግኘት የሚጥረውን ባለሥልጣን ኢንፌክሽኑ ሰው አስተላልፈብዎት እንዳይሆን - ወይንም እርስዎ ወደ ሌላ ሰው አስተላልፈው እንዳይሆን - የሚጠረጥርዋቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ማሳወቅ ማለት ነው። አብረዋቸው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙት ግለሰዎች ወይም አብረዋቸው መርፌ የተካፈሉ ሰዎች፤ አንዳንድ ጊዜም የቤተሰብ አባሎች ሊሆኑ ይችላሉ። ዓላማው ሁሉም ኢንፌክሽን ያላቸው ማግኘት ነው። የኢንፌክሽን ምንጭ መፈለግ በምስጢር (sekretess) የሚከናወን ሥራ ነው። ማንነትዎ አብረዋቸው ግኑኝነት ለፈጸሙት ሰዎችን አይነገርም። ከሌሎች ሰዎች እንደገና በግብረ-ሥጋ በመገናኘትዎ በሽታው የተላለፈባቸው ሰዎች እንዳይኖሩ ጥርጣሬ ካለ: የኤችአይቪ የኢንፌክሽንን የመፈለግ ሥራው ይደገማል።

### ወደ ሌሎችን ላለማስተላለፍ መከተል የሚገባዎት የጽዳት ምክሮች

- ትንሽ ቁስል ካለብዎት መሸፈኛ ያድርጉበት።
- የቁስል ጨርቅ ለመቀየር ሰው ካገዝዎት: አጋዡ የፕላስቲክ ጓንቲ መጠቀም አለበት።
- በደም የተበከለ ማተሪያል (ጨርቅ ወረቀት ወዘተ) ከመጣልዎ በፊት በደንብ ይጠቅልሉ።
- በደም የቆሸሸ ልብስ ባጣቢ ማኪና ይታጠባል።
- የደም ጠብታ: ለምሣሌ በወለል የነጠበ: በወረቀት ተወልውሎ ይጣላል። ከዛ በህዋላ በሳሙናና በውኃ በደንብ ይታጠቡ።
- አንድ ግለሰው በቆዳ ቁስሉ: በዐይኑ: ባፍንጫው ወይም በአፉ ደም ከነጠበበት: በተሎ መታጠብ አለበት። ግለሰዉ: ደሙ ኢንፌክሽን እንዳለበትና በተሎ ወደ ኢንፌክሽን ክሊኒክ መሄድ እንዳለበትም ይነገራል።

### ወደ ሌሎች ኢንፌክሽን ላለማስተላለፍ ሀኪምዎ የሚሠጥዎት መመሪያዎች

- ሀኪሙ አስፈላጊ ነው የሚለውን ምርመራ ለማድረግ የግድ በቀጠሮ መምጣት አለብዎት።
- በኤችአይቪ ኢንፌክሽን ከተለከፉ: ማንኛውም ለኤችአይቪ ኢንፌክሽን አደጋ በይበልጥ የሚያጋልጠውን (ታች ይመልከቱ) ግብረ-ሥጋ ከመፈጸምዎ በፊት: ከርስዎ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽመውን ግለሰው: ማሳወቅ (የማሳወቅ ግዴታ) አለብዎት። የብልት: የአፍና የፍንጥጣ ወሲብ በሚፈጸምበት ወቅት የኤችአይቪ ኢንፌክሽን አደጋ አለ።
- የወንድ ብልት በሴት ብልት: በፍንጥጣና በአፍ አስገብቶ የሚፈጸም ግብረ-ሥጋ: ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ኮንዶም መጠቀም ይገባል።
- አደንዛዥ ዕጽ በመርፌ የሚወጉ ከሆነ: የብቻዎን መርፌን ይጠቀሙ፤ የርስዎ መርፌዎች ሌላ ሰው እንዲጠቀም አይፍቀዱ። የድራግ ማዘጋጃ ዕቃ በጋራ አይጠቀሙ። የመውግያ መርፌ ለኢንፌክሽን አደጋ በማያደርስበት ቦታ ይቀመጥ።
- ደም: የወንድ ዘር(ስፐርም): እንቁላል ወይም ያካል ክፍል ለፍልሰት (transplantation) መለገስ አይፈቀድልዎትም።

- የጥርስ ወይንም ሌላ ዓይነት ህክምና ሲያደርጉ የኤችአይቪ ኢንፌክሽን እንዳለዎት ማሳወቅ ግዴታዎ ነው።
- መነቀስ ከፈለጉ፤ ጆሮዎን ወይም ሌላ ያካል ክፍልዎን መበሳት (piercing) ከፈለጉ፤ ወይም ሌላ ደም የሚያስፈስስ ሹል እቃ የሚጠቀሙ ከሆነ፤ ጉዳዩ ከመጀመሩ በፊት ደምዎ የኤችአይቪ ኢንፌክሽን እናዳለበት ማሳወቅ አለብዎት።
- እንደ ምላጭና የጥርስ መፋቂያ የመሣሠሉት በሽንት ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን ከሌሎች አይጋሩ።
- በሥራ ቦታ ወይም በሌላ ለኤችአይቪ አደጋ የሚያጋልጥ ቦታ: ሥራ ካለ: ሊገደቡ ይችላሉ።

በስዊድን ኢንፌክሽን ህግ መሰረት: ኤችአይቪ ለሕብረተሰቡ አደገኞች ከሆኑ በሽታዎች (allmänfarlig sjukdom) አንዱ ነው። ሀኪምዎ የሚሠጥዎትን ምክር ተከትለው ወደ ሌሎች ሰዎች ላለማስተላለፍ የመከላከል ግዴታ አለብዎት።

እዚህ ላይ በሚጠቀሰው መመሪያ ”ይበልጥ ለአደጋ የሚያጋልጥ” የሚል አገላለጽ አለ፤ በኢንፌክሽን ህግ ተጠቅሶም እናገኘዋለን። ይኸም ማለት: አሳንሶ ማየት የማይገባ እውነተኛ አደጋ ማለት ነው። ደንበኛ ህክምና የሚደረግልዎት ከሆነ: እና ሌላ የኢንፌክሽን አደጋ የሚጨምር ሁኔታ ካልተከሰተ: ኢንፌክሽኑን የማስተላለፍ አደጋ ትንሽ ስለሆነ አሳሳቢ አንዳልሆነ ሀኪምዎ ሊገመግም ይችላል። ያኔ: የማሳወቅ ግዴታዎን የሚመለከተው መመሪያ: ህክምና የሚሠጥዎት ሀኪም በድጋሚ ሊገመግመው ይችላል። በሚኖሩበት አውራጃ (län) ያለው የኢንፌክሽን መከላከያ ሀኪምን (smittskyddsläkaren): የተሠጠዎትን መመሪያ በድጋሚ እንዲያይ መጠየቅም ይችላሉ። ግምገማው እስኪገባደድ ድረስ ግን የተሠጠዎትን መመሪያ ይከተላሉ።

የሆነ ዓይነት መመሪያ ቢከተሉም: አሳሳቢ የኢንፌክሽን አደጋ ካጋጠመ፤ ወይም እንዳያጋጥም ሥጋት ካለ፤ ሁልጊዜ የሚመለከተውን አካል ማሳወቅ አለብዎት። ይህን ጉዳይ አንስተው ሀኪምዎን ያነጋግሩ።